# ዜና ስለ ራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት

ዜና ሰልፍ ሰፐላይ በየሁለት ወሩ አንዴ በ ሰልፍ ሰፐላይ ግብረ ሐይል በኢትዩጵያ አማካይነት የሚዘጋጅ ሲሆን ይህም ግብረ ሐይል በመንግስት ተቋማትና ከልማት አጋሮች የተወጣጣ ፎረም ነው፡፡ የጃይካ ዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት ዜና በማዘጋጀት ረገድ ቅድሚያውን ወስዷል፡፡

## ማውጫ

የላይኛው መልዕክት
- መልዕክት ከአዲሱ የደቡብ ክልል የመጠጥ ውሃ ተቋ/አስ/መሳ/ጥገና ዋና የስራ ሂደት ባለቤት ከአቶ ካሳሁን ወ/ ጊዮርጊስ ቴቃ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ

ከአቻ አጋሮች እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች
- ትምርታዊ ጉዞ በሰልፍ ሰፐላይ ዙሪያ በብታጅራ
- ራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት ቅድመ ጥናት
- ራስ አገዝ የውሃ አቅርቦትበተንዛንያ 4000 የባለገመድ ፓምፖዎች
- ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ቁርጠኛ ነው
- ‘የውሃን አከባቢ ማፅዳው ለጠናዩስል ነው
- የባለ ገመድ ፓምፕ ተጠቃሚዎች ድምፅ
- ጥሩ ተሚክሮ በሀይጅንና ሳንቴሽን
- የገመድ ፓምፕ ስታንዳርዴሽን በመጠናቀቅ ላይ ነው

ማስተወቂያ /መረጃ/
- ዜና በብሔራዊ ሰልፍ ሰፐላይ ግብር ሐይል
- ክንውኖች

## መልዕክት ከደቡብ ክልል ውሃ መስኖ ልማት ቢሮ




“ራስ አገዝ ማለት በራስ አቅም ወይም በአጭሩ በራስ ወጪ የውሃ ተቋማት መገንባት ነው፡፡” ይላሉ አቶ ካሳሁን ወ/ጊዮርጊስ ቴቃ የመጠጥ ውሃ ተቋ/አስ/መሣ/ጥገና ዋና የስራ ሂደት ባለቤት “በመጀመሪያ ደረጃ በራስ አቅም መገንባት ሲባል አነስተኛ የውሃ አቅርቦቶችን ማለትም ማህበረሰብ አቀፍ የውሃ ተቋማት አነስተኛ ምንጮች ማለትና እንዲሁም የባለ ገመድ ፓምፕ ስርጭትን ይመለከታል፡፡

”ሲቀጥሉ አቶ ካሳሁን “የራስ አገዝ ውሃ አቅርቦትዕድገትን በባለገመድ ፓምፕ ስናየው በተለያዩ ምክንያቶች ዕድገቱ አዝጋሚ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ለምሳሌ የማምረት አቅም እና የጥራት ውስንነቶች በአምራቾች በኩል ትልቁ እና ዋናው ችግር ሆኖ ላለፉት ሁለት አመታት ቆይቷል፡፡ይህ በዋናነት በ10000 የባለገመድ ፓምፕ ጋር ተያይዞ ያለ ችግር ነበር፡፡


የክልሉ ውሃ ቢሮ ተረክቧቸው የሚገኙ የባለገመድ ፓምፖዎች

ሆኖም ግን በዚህ የበጀት አመት አብዛኞቹ በተለያዩ በክልሉ በሚገኙ ቦታዎች ለማስተከል ዕቅድ ይዘናል፡፡እስከ አሁን ባለው ሂደት 8500 የባለ ገመድ ፓምፕ ወደ ዞኖች ከዛም ወደ ወረዳዎች ተሰራጭተዋል፡፡

ስለዚህ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ / GTP-2/ መጨረሻ የንፁህ ውሃ ሽፋንን አሁን ካለበት 67% ወደ 100% ለማድረስ ተስፋ እናደርጋለን፡፡በተመሳሳይ መልኩ የንፁህ ውሃ አቅርቦት ላልደረሰበት 20% የሚሆነውን የገጠሩ ህዝብ በራስ አገዝ ጭምር እናደርሳለን ብለን እናምናለን ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በንፁህ ውሃ አቅርቦት እና ሽፋን ትልቅ እርምጃ ወደ ፊት እንደ ማለት ነው፡፡


የክልሉ የገመድ ፓምመፐዎች ወደ ዞኖችና ወረዳዎች ለማሰራጨት ሂደት ላይ

(ፎቶ ዋስ - ሮፕስ)

በዚህም እምረታ ወደ 28000 ሲኪሞች (ተቋማት)ማድረስ ይቻላል ማለት ነው፡፡እንደ ጃይካ ያሉ የባለ ድርሻ አካላት ሚና በክልሉ በመጠጥ ውሃ አቅርቦት እየተጫወቱት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ይህ ተሳትፎአቸውም በጣም ጠቃሚና ብዙ ቅንጅታዊ ስራዎች እና ልምድ ለመለዋወጥና በፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን ግብ ለመምታት ያስችላል፡፡

ክልሉ የተለያዩ ስራዎችን በተገኙ መንገዶዎች እና አማራጮች በመጠቀም የወረዳው የዋሽ ቡድን ተጨምሮበት ህብረተሰቡን የመቀስቀስና የማነሳሳት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

አቶ ካሳሁን በራስ አገዝ ዙሪያ አስተያየታቸውን ሲሰጡ “ትክክል ነው፡፡ በጣም የሚታወቁና ግልፅ የሆኑ ተግዳሮቶች በኛም በኩል ይስተዋላሉ፡፡ ለምሳሌ የሰለጠነ ባለሙያ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ከመቀበል የለው ተግዳሮት አንፃር የውሃ ጥራት ጉዳይ እና ሃይጅንና ሳንቴሽን ትምህርቶችን በስፋት መስራት ናቸው፡፡

# የራስ አገዝ ተቋማት የመማማሪያ ጉብኝት በቡታጂራ ተደረገ

Millennium Water Alliance



በራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት ዙሪያ የሚሰሩ ወኪሎች እና የሚሊኒያም ዋተር አጋሮች በቡታጅራ እ.ኤ.አ ከመስከረም 07-09 2015 ትምህርታዊው ጉብኝት ውይይት አድርጓል፡፡ይህ ትምርታዊ ጉብኝት የተዘጋጀው ከውሃ መስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚኒስተር መስሪያ ቤት ፤ ከአይ አር ሲ /IRC/ እና ሚሊንየም ዋተር አሊያንስ ጋር በቅንጅት በመሆን ነው፡፡ በትምህርታዊ ውይይት ሀገራዊና ክልላዊ የራስ አገዝ የውሃ ተቋማት የግንባታ እንቅስቃሴዎች የቀረቡ ሲሆን የተገኙ መልካም ልምዶችና የገጠሙ ችግሮች በተሳታፊዎች ውይይት ተደርጓል፡፡

ከሀገር አቀፍ ራስ አገዝ ግብር ሀይል እና ክልላዊ የድርጊት እና የኔትዎርክ አሰራር ጋር እንዴት መስራት እንዳለባቸው ተማከረዋል፡፡

ተሳታፊዎቹም በጃይካ ዋስ ሮፕስ ፕሮጀክት ድጋፍ እየተሰሩ የራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት ግንባታ በቤተሰብ ደረጃ እየተከናወኑ ስላሉ ስራዎች የመስክ ጉብኝት በማድረግ ተጠናቋል፡፡

(http://www.ircwash.org/blog/learning-butajira-capital-self-supply)

# ዜና ከብሔራዊ የራስ አገዝ ውሃ አቅርቦትግብረ ሀይል

ብሔራዊው የራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት ግብር ሀይል ውይይት እ.ኤ.አ በ ጥቅምት 8 እና በህዳር 13 2015 ተካሄዶል፡፡ የግብረ ሀይሉ ዋና የውይይት ርዕስ የነበረው የራስ አገዝ ሂደትን የእርስ በእርስ ግንኙነት እና ቅስቀሳ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡

## የራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት በ4000 የገመድ ፓምፕ በ ታንዛኒያ

በራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ ሀገራትከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ እንደ ምሳሌ ታንዛኒያን ልናይ እንችላለን፤፤ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና የገመድ ፓምፕ ፎረም በቅርብ ጊዜ እንዳሳወቀው 4000የገመድ ፓምፖች ተገዝተው በአባወራዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ይህ ፎረም የተዘጋጀው በ ዊንሮክ ታንዛ-ኒያ በዩስ ኤድ የሚደገፍ ድርጅትና ከ ገመድ ፓምፕና በእጅ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ካምፓኒ 70 ሰዎች ነው፡፡

ሺፖ(SHIPO)በኔዘርላንድ የሚደገፍ ድርጅት ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የገመድ ፓምፕንና ሮታ ስለጅ የእጅ መቆፈሪያ (Rota sludge manual drilling) በታንዛኒያ ያስተዋወቀው እ.ኤ.አ በ 2005ዓ.ም. ነበር፡፡ በአሁን ሰአት ሺፖ(SHIPO) ስማርት(SMART) የተባለ ማእከልን በውሃ ጉድጓድ፣ቧንቧ፣በውሃ ጉድጓድ ማገገም፣ በአባወራ ደረጃ ውሃን ማጣራት እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎችን በማምረትና በቢዝነስ እውቀት በሰለጠኑ የአካባቢ የግል ድርጅቶች እንዲሰራ እያደረገ ይገኛል፡፡ በአለፈው አመት ሺፖ(SHIPO) ከ ዊንሮክና ከ ስካት(SKAT) ፋውንዴሽን እርዳታ አግኝቶ ነበር፡፡

ከ10 አመት ስልጠና በኋላ በውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ የተሰማሩና 10.000 የገመድ ፓምፕ ያመረቱ 30 አነስተኛ ተቋማት በአሁን ሰአት ሊፈጠሩ ችለዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 60% ለማህበረሰቡ በተለይም ለአነስተኛ የገጠር ማህበረሰብ ተተክሏል፡፡የተቀረው 40% ለራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት በከተማዳርቻ በሚገኙ አባወራዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በአብዛኛው ጊዜ አባወራዎች ቀጥታ የገመድ ፓምፐን ከ አምራቾች ሲገዙ አንዳንድ ጊዜ ግን በአነስተኛ ብድር ገዝተው ይጠቀማሉ፡፡ ስለ ስማርት ማእከል (SMART Centre) መረጃ ለማግኘት ይህን ድህረ ገፅ ይጎብኙ www.shipo-tz.org



ለአነስተኛ መስኖ የገመድ ፓምፐን ሲጠቀሙ (ግፊትን በመጠቀም ውሃን በቀጫጭን ቱቦ ማስተላለፍ)



መኪና አጣቢዎች የገመድ ፓምፐን በመጠቀም ውሃ ከውሃ ጉድጓድ ሲያወጡ

## ለራስ አገዝ የውሃ ተቋማት የሚረዳ ቅድመ ጥናት ተደረገ

**Millennium Water Alliance**

ሚሊኒየም ዋትር አሊያንስ ከአይ አር ሲ እና ከአኳ ፎር ኦል በጋራ በመሆን ፕሮጀክቶች በሚሰሩበት ወረዳዎች የቅድመ ጥናት ስራ ፕሮጀክቶች በሚሰሩበት ወረዳዎች ተካሄዷል፡፡ከቤት ለቤት በተጨማሪ የቡድን ቤቶች ጥናት የራስ አገዝ ትኩረት አቅጣጫ ነበር፡፡የቡድን የራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት ግንባታ እስከ ዛሬ ሲተገበር የቆየው ለሁለቱም ማለትም በመንግስትና በግበረ ሰናይ በ ነፍስ ወከፍ ሊያወጣ የሚችለው ዋጋ ትንተና ጥቅሙና አቅራረቡ ታይቷል፡፡ይህ ቅድመ ጥናት ለፕሮጀክቶች መረጃ ለማቅረብ እና የራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት ክትትል ሊጠቅም እንደሚችል ይታመናል፡፡የመጀመሪያውና የጥናት ውጤት የሆነው የአሞናዳ ወረዳ በፖስተር መልክ ታትሞ ወጥቷል፡፡ተጨማሪ መረጃ በየ ድርጅቶቹ ድህረ ገፅ ማግኘት ይቻላል፡፡

http://www.ircwash.org/resources/poster-my-water-my-business-monitoring-self-supply-rural-ethiopia.

# አሞ ማይክሮ ፋይናንስ በቁርጠኝነት ይሰራል




አቶ ሙሉጌታ ከ ዋስ ሮፕስ ፕሮጀክት ቡድን አባላት ጋር (ፎቶ ከዋስ ሮፕስ)

በቅርቡ በፕሮጀክቱ ታርጌት ወረዳዎች የመስክ ምልከታ እና ግምገማ ተደርጎ ነበር፡፡ የዋስ ሮፕስ ቡድን አባላት ከአሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ጥሩ የሆነ ተሞክሮ አግኝቷል፡፡

በዚህም የይርጋጨፌ ወረዳ ብድር አመላለስ በጥሩ ተሞክሮነት አይተነዋል፡፡ በመስክ ምልከታ ወቅት አቶ ሙሉጌታ የወረዳው አሞ ማይክሮ ፋይናንስ ጀነራሊስትን አነጋግረናቸው ነበር፡፡

ከዚኛው የበጀት አመት ብቻ ግማሽ የባለ ገመድ ፓምፕ ብድሩን ወደ አካውንታቸው ለማስመለስ ዕቅድ ይዘዋል፡፡እንደ አሞ ይህን ብር ለማስመለስ ቁርጠኝነቱ አለ፡፡

ይህን ምናደርግበት ዋናው ምክንያት ምን ያህል ገንዘብ በባለ ገመድ ፓምፕ ተይዞ እንዳለ እንድናውቅ ነው፡፡ ይህ ብር ቢመለስ ብሩን ለሌሎች ፕሮግራሞች እንደ ዘር ብር መጠቀም ያስችላል ይላሉ አቶ ሙሉጌታ ይህን የማስመለስ ዘመቻ ባለፈው የበጀት አመት ጀምረናል፡፡በዚህ አመት ደግሞ ብድር የማስመለሱ ስራ ዋናው አጀንዳችን ይሆናል፡፡ይህንንም ስራ ከወዲሁ ጀምረናል፡፡በርግጥ የተወሰኑ የባለ ገመድ ፓምፕ ተጠቃሚዎች በጥቂቱም ቢሆን መክፈል ጀምረዋል፡፡ በዚህም የተወሰኑ ተጠቃሚዎች 500 ብር ያህል ከፍለዋል፡፡ ምን አልባትም በሚቀጥለው ጥቂት ወራቶች ውስጥ መጥታችሁ ሁኔታውን ብትመለከቱት የተለየ ገፅታ ይኖረዋል፡፡

ብድሩንም አብዛኞቹ የባለ ገመድ ፓምፕ ተጠቃሚዎች መክፈል የጀመሩ በመሆኑም ብዙም ችግር አይገጥመንም ይህ የኛ ስራ ነው፤ የኛ ገንዘብ ነው ፡፡

ስለገጠማቸው ችግሮች ሲያብራሩ መጀመሪያ አካባቢ አንድ ሁለት ያህል ችግሮች ነበሩ ዋናው ችግር ግን የአመለካከት ክፍተቱን መድፈን ነው፡፡የጥገኝነትና የአመለከካት ለውጥ አለመኖሩ ችግሩን አባብሶት ነበር፡፡

ብዙ ሰዎች  የባለ ገመድ ፓምፕ ከጃፓን መንግስት በነፃ የተሰራጨ ይመስላቸው ነበር፡፡ በዚህ የሕብረተሰብን አመለካከት መቅየር አስቸጋሪ ነበር፡፡ በኋላ ላይ ግን የቀበሌ አስተዳደሩን አካተን መስራት ከጀመርን በኋላ ነገሮች መልክ መያዝ ፍሬ ማፍራት ጀምረዋል፡፡ዛሬ ብዙ ነገር ተለውጧል፡፡

ሕብረተሰቡም ግንዛቤ ጨብጧል፡፡ ለተለያዩ ተግባራት ስንመጣ  ከተለያዩ የባለ ድርሻ አካላት ጋር በተለይም ከውሃ እና ከሕብረተሰብ ጋር ከሚሰሩ የኤክስቴንሽን ሰራተኞች ሰነዶችን በስርዓትና ባግባቡ አለመያዝ ችግር ነበር፡፡አንዳንድ የባለ ገመድ ፓምፕ ተጠቃሚዎች እኛ መረጃ በሰነድበደንብ ሳናቀርብላቸው ተከላ ሁሉ አድርገው ነበር፡፡ይህ ሁሉ በጣም ችግር ፈጥሮብን ነበር፡፡ አሁን ግን ሁሉም ነገር መልክና መስመር ይዞ ተስተካክሏል፡፡


አቶ ሙሉጌታ በስተቀኝ በተከላ የሚገኘውን የገመድ ፓምፕ በመጎብኘት ላይ

አቶ ሙሉጌታ የሚከተለውን መልዕክት በማስተላለፍ ቃለ ምልልሱን አጠናቀዋል፡፡ እኛ እንደ አሞ ማይክሮ ፋይናንስ ሰራተኛ በመጀመሪያ ደረጃ ማወቅ ያለብን በባለ ገመድ ፓምፕ ምክንያት የምንጠቀመው ጥቅም  አለ፡፡

የፋይናንስ አቅም ከመፍጠር በተጨማሪ የተገኘውን ገንዘብ እንደ ዘር በመጠቀም ለሌሎች ተመሳሳይ ፕሮግራሞች መጠቀም ያስችለናል፡፡ በግሌ እንደሚገባኝ ይህ በጣም ጠቃሚና  የአሞ ማይክሮ ፋይናንስ ሰራተኞች መረዳት ያለብን ይመስለኛል፡፡ይህ ብዙ ገንዘብ በተለያዩ መንገድ ለሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ለመጠቀም ያስችለናል፡፡

ይህን ጉዳይ በአግባቡ ከተረዳን ገንዘብን መሰብሰብ ችግር የሚሆን አይመስለኝም፡፡

# “ለጤንነቴ ስል የውሃውን አካባቢ አፀደዋለሁ”

## መልካም ተሞክሮ ከባለ ገመድ ፓምፕ ተጠቃሚ ቃለ ምልልስ በዋስ ሮፐስ !

የገጠር የንፁህ ውሀ አቅርቦት በባለ ገመድ ፓምፕ ስርጭት በራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት ዘዴ አስቸጋሪ ቢሆንም ይህ ማለት ግን ሁልጊዜ ትክክል ላይሆን ይችላል፡፡

አቶ ገረመው ሂዲሞ በዳሌ ወረዳ በቤራ ጠድቾ ቀበሌ ነዋሪ እና የባለ ገመድ ፓምፕ ተጠቃሚ ናቸው፡፡የፓምፑን አካባቢ በማፅዳት ረገድ አርአያ ናቸው፡፡

እኚህ ሰው አርሶ አደርና የቀድሞ ወታደር ሲሆኑ የፓምፖችን አካባቢ በአጥር ከልለው ከሰው እና ከእንስሳ ንኪኪ ፍፁም ንፁህ አድርገው የተሻለ የውሃ ጥራት እያገኙ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ “ከጥቂት አመታት በፊት ለወታደራዊ ግልግሎት ሰሜን ኢትዮጵያ በነበርኩበት ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ የባለ ገመድ ፓምፕ አየሁ፡፡ ነገር ግን ይህ የባለ ገመድ ፓምፕ በቀላሉ የሚመረት መሆኑን አላውቅም ነበር፡፡

ከዛ መልስ እኔ እና ባለቤቴ ተማክረን ይህን ቴክኖሎጂ ለመግዛት ወሰንን ቡዙም ሳንቆይ እዚሁ በራችን ላይ ቴክኖሎጂውን አስተከልን፡፡ ካስተከልን በኋላም ፓምፑን መከባከብና ንፅህናውን መጠበቅ ለኛ ብዙም አስቸጋሪ አልነበረም፡፡ምክኒያቱም ንፁህ ውሃ ማለት ጤናማ ህይወት ማለት ነው፡፡ የዚህ ሁሉ ምክንያት እንግዲህ ይህ ነው፡፡” ይላሉ አቶ ገረመው በቅርብ በወረዳው ከፕሮጀክትና ከክልሉ ውሃ ቢሮ ጋር በተደረገው የውሃ ጥራት ምርመራ የአቶ ጌታቸው የጉድጓድ ውሃ ከ ኢ- ካይ ነፃ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

የፓምፑን አካባቢ የማፅዳት ስራ ከቤተሰቦቼ ጋር ተራ በተራ እናደርጋለን፡፡ እኔ በማልኖርበት ጊዜ ባለቤቴ የፓምፑን አካባቢ እንክብካቤ ታደርግለታለች፡፡በአጋጣሚ ሁለታችንም በማንኖርበት ጊዜ ልጆቻችን የማፅዳቱን ስራ ይሰራሉ፡፡ ቀላል ነው፡፡አጥር ለማጠር ያወጣነው ገንዘብ የለም ሁሉም ነገር አካባቢዩ ካሉት አማራጮች ነው፡፡የተጠቀምኩት ዘዴ ገንዘብ የሚያስወጣ እንኳን ቢሆን ለመጠቀም ዝግጁ ነኝ፡፡

“ሰዎች እኔ የማደርገውን አይተው ልምድ ቢወስዱ ደስተኛ ነኝ፡፡” ይላሉ አቶ ገረመው በማጠቃለያቸውም ጤናችን በእጃችን ነው፡፡ ይህ ውሃ ነው በብዙ መንገድ ሊበከል ይችላል፡፡በጤና ኤክስቴሽን ሰራተኞች የገመድ ፓምፑን ንፅህና ለመጠበቅ የተወሰኑ ስራዎች እንዲሰሩ ተነግሮኝ ነበር፡፡በፓምፑ ዙሪያ ስላለው ንፅህና የአካባቢ ፅዳት ከተነገረኝ ጀምሮ እየተገበርኩ ነው፡፡



አቶ ገረመው ሐድመ በመሀከል ሆነው ከእንጨት የሰሩትን ባለ ገመድ ፓምፕ የሚያደርጉትን እንክብካቤ በማሳየት ላይ

(ፎቶ ከዋስ ሮፐስ)

## በኢትዮጲያ የዛሬ አስር አመት በጃይካ ሲተዋወቅ የነበረው የገመድ ፓምፕ የጥራት አወጣጥ ክንውን በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

**JICA WAS-RoPSS**

በገመድ ፓምፕ የጥራት ደረጃ አወጣጥ ሂደት ላይ በተደረገው ተከታታይ ውይይት ላይ የተሳተፉት ቴክኒካል ቡድኑ የተውጣጡት ከግል አምራቾች፣ የአገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የመጡ የገመድ ፓምፕ ስፔሻሊስት ይገኙበታል፡፡

የገመድ ፓምፕ የጥራት ደረጃ ማውጣት ማለት አንድ የተወሰነ የገመድ ፓምፕ ሞዴል እንዲኖር ማድረግ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ሞዴሎች ያን የተወሰነውን የገመድ ፓምፕ ጥራት ደረጃን የሚያሟሉ እንዲሆኑ ሲሆን  የቴክኒካል ቡድኑ ያደረገው የገመድ ፓምፑ የተለያዩ ክፍሎች መጠንና የገመድ ፓምፕን ለማምረት የሚጠቀሙባቸውን እቃዎች(ማቴሪያል) ጥራትና ደረጃ ማውጣት ሲሆን ይህም የ ዋስሮፕስ ፕሮጀክት ዋና አላማ ነው፡፡

እነዚህ ለጥራት ደረጃ የሚጠቅሙ ቅድመ ሁኔታዎች ተጠናቀው ለውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር እ.አ.አ በሐምሌ 2015 ያስረከብን ሲሆን በአሁን ሰአት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለኢትዮጵያ ጥራት ደረጃ ኤጀንሲ ጥያቄ አቅርቦ ያስፈፅማል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

### እ.ኤ.አ በጥቅምት እና በህዳር 2015 የተሰሩ ስራዎች

| | | |
|---|---|---|
| መስከ | 7–9 | የራስ አገዝ ትምህርታዊ ግብኝት በቡታጅራ |
| መስከ | 15–17 | የፕሮግራም ማኔጅመንት ስብሰባ በአሶሳ የሰልፍ ሰፕላይ ስትራቴጂ ክለሳ ማድረግ |
| ህዳር | 26–30 | 26-30 2015 (እ.ኤ.አ)የውሃ እና ጤና ኮንፍረንስ ዩኒቨርስቲ ኦፋ ኖርዘርን ካሎራይና ቻፕል ሂል |
| ህዳር | 12 | የባለ ገመድ ፓምፕ አጭር መፅሀፍ የንድፍ ስብሰባ/ዋስ ሮፕስ/ |
| ህዳር | 19 | የባለ ገመድ ፓምፕ አምራቾች ተካዮች እና የአሰራርና ጥነና ማንዋል ላይ የተደረገ ዋርክ ሾፕ |
| ህዳር | 20 | የባለ ገመድ ፓምፕ ተከላ የቼክ ሊስት ወርክ ሾፕ |

### እ.ኤ.አ በታህሳስ 2015 እና ጥር 2016 የሚሰሩ ስራዎች

- ቅድመ የራስ አገዝ ጥናት በዱግዳ ወረዳ ዳታ ክሊንግ ትንተና መስጠትና መፃፍ
- ቻሌንጅ ፈንድ ዲዛይን ማድረግ ማስተዋወቅ በተለይም ለግሉ ዘርፍ ከራስ አገዝ ጋር በተያያዘ
- የራስ አገዝ ቤዚላይን ጥናት ለ 5 ወረዳዎች አማራ ክልል ዳታ ክሊንግ ትንተና መስጠት እና መፃፍ
- ከአማራ ብድርና ቁጠባ ጋር በራስ አገዝ ዙሪያ የቡድን ውይይት ማድረግ
- ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም የገበያ ጥናት እና ምርት ማምረት በተለይም በራስ አገዝ ላይ
- የ 10000 የባለ ገመድ  ፓምፕ ማስተዋወቅ የመግቢያ ስራዎች መስራት የጠጋኞች ስልጠና መስጠትና ድጋፍ ማድረግ
- የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ፕሮግረስ ስብሰባ
- የባለ ገመድ ፓምፕ የማህበረሰብ አቀፍ የማስተዋወቅ ስብሰባ ለአከባቢ ባለሙያዎች ከቢዚነስ አንፃር

If you have any comments, questions, suggestions, please contact us at;

WAS-RoPSS Project
Room # 012, Ministry of Water, Irrigation and Energy
Tel: +251 - (0)11-651-1455
Mob: +251 - (0)935-353210/12/14
E-mail : jica.ropepump.ethiopia@gmail.com

Websites

【JICA】 http://www.jica.go.jp/oda/project/1100485/index.html (Japanese)
http://www.jica.go.jp/project/english/ethiopia/004/index.html (English)
【MoWIE】 http://www.mowr.gov.et/
【IRC】 http://www.ircwash.org/
【A4A】 http://www.aquaforall.org/
【RWSN】 http://www.rural-water-supply.net/en/resources/details/662
(Self supply fair presentations are available!)